## *በኦሮምያ ደኖች ላይ በወያኔዎች የተለኮሰውን እሳት ለማጥፋት ሁሉም ይረባረብ*

*የወያኔ መንግስት ከኣስር ኣመታት በፊት እንዳደረገው ሁሉ ዛሬም በኦሮምያ ደኖች ላይ እሳት ለኩሶ እያነደደ ነው። በጥፋት ፖሊሲው እንደ ገፋ የሚገኘው ይህ መንግስት በተለይም ኦሮምያን ዶግ ኣመድ ለማድረግ ኣቅሙን ኣሟጥጦ እየሰራ ይገኛል። ከደቡብ ምስራቅ ኦሮምያ የሚወጡ ተጨባጭ ምንጮች እንዳረጋገጡት ከኣርሲ ዞን እስከ ባሌ ተራሮች ተንጣልለው የሚገኙ ብርቅዬ የኦሮምያ ደኖች የወያኔ መንግስት እሳት ሰለባ እየሆኑ ናቸው። በስርኣቱ ወኪሎች እንደተለኮሰ በተረጋገጠው በዚህ እሳት የጢዮ፣ የዳጋሉ ጢዮ፣ የካካ፣ የገላና፣ የጋራ ዶሮ፣ የኮፈሌና የበቆጂ ተራሮችን የሸፈኑ የኦሮምያ ደኖች በኣሳሳቢ ሁኔታ እየነደዱ ናቸው። በተለይም የዶሮ ተራራን የሚሸፍነው ደን በከፋ ሁኔታ ነዶ ወደ ኣመድነት እየተቀየረ መሆኑን ምንጮቹ ያመለክታሉ።*

*እንደሚታወቀው ሁሉ የወያኔ መንግስት እነዚህን የደቡብ ምስራቅ ኦሮምያ ደኖችን ሆን ብሎ እያቃጠለ የሚገኘው በኦሮሞ ህዝብና በኦሮምያ ተፈጥሮኣዊ ልምላሜ ላይ ካለው ጠላታዊ ስሜት መሆኑ የሚያጠያይቅ ኣይደለም። ለስርኣቱ ካድሬዎች ቅርበት ካላቸው ምንጮች ኣፈትልከው የሚወጡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ደግሞ ለቃጠሎው የተሰጠው ሰበብ ኣሳማኝነት ያለው ኣይደለም። የእስልምና ኣክራሪ ሃይሎች በደኑ መሽገው ሊያጠቁን እየተዘጋጁ ናቸው፣ ኦነግም ለረጂም ጊዜ በጫካው ተጠልሎ ሲወጋን ኖሯል የሚሉና ሌሎች ተልካሻ ምክንያቶችን እየደረደሩ የተፈጥሮ ሃብትን ማውደም ለዘመናት የዘለቀው የስርኣቱ ጠላታዊ እርምጃ እንጂ ሌላ ኣዲስ ትርጉም ሊሰጠው የሚችል ኣይደለም።*

*ይህ ፀረ ኦሮሞና ፀረ ኦሮምያ የሆነ ስርኣት ከኣስራ ሁለት ኣመታት በፊትም የባሌ፣ የቦረና፣ የሓረርጌ፣ የወለጋና የጅማ ኣካባቢ ደኖች ላይ በማን ኣለብኝነት እሳት ለኩሶ ማውደሙ የሚታወስ ነው። በዚያ ወቅትም ኦነግ በነዚህ ደኖች መሽጎ ይወጋናል በሚል ተልካሻ ምክንያት የኦሮምያና ከኦሮምያም ኣልፎ የክፍለ ኣህጉሩን የተፈጥሮ ሃብት የሆነውን የተፈጥሮ ደን ኣራቁቶ በረሃማነት እንዲስፋፋ የበኩሉን ኣፍራሽ ሚና ተጫውቷል። እስከ 500 ኣመት እድሜ ያላቸውን ዛፎች ያቀፉ እነዚህ ብርቅዬ ደኖች በነደዱበት በዚያ ወቅት በፊንፊኔ ዩኒቨርሲቲና በሌሎችም የሃገሪቷ ዩኒቨርሲቲዎች የሚማሩ የኦሮሞ ተማሪዎች ትእግስታቸው ተሟጥጦ የበኩላቸውን እርምጃ መውሰዳቸው ኣይዘነጋም። ተማሪዎቹ ምንም ኣይነት ርቀት ሳይገድባቸው እሳቱን ለማጥፋት መዝመታቸውና ሰላማዊ ሰልፍም ጭምር በመውጣት ለውድመቱ ተጠያቂ የሆነውን የወያኔ መንግስት ማውገዛቸው ሁሌም በጀግንነት የሚዘከር እርምጃ ነው።*

*ለመሆኑ የወያኔ መንግስት እየተመላለሰ የኦሮምያ ደኖችን የሚያቃጥልበት ዋነኛው ምክንያት ምንድነው? እሳቱን ለማጥፋት የሚረባረቡ ዜጎችንስ ለምን ሌላ ስም እየለጠፈባቸው ያስራል ያስፈራራል? የጥያቄዎቹ ምላሽ ግልፅ ነው። ስርኣቱ መንግስታዊ ሃላፊነቶችን መሸከም የማይችልና በተለይም የኦሮምያ ተፈጥሮኣዊ ልምላሜ መልኩን ጠብቆ እንዲቀጥል ፍላጎት የሌለው በመሆኑ ነው። የዘረፋ ፖሊሲውን ብቻ ተግባራዊ ለማድረግ ኣቅዶ ሸገር ቤተ መንግስት የገባው ይህ*

ቡድን ልማታዊ መንግስት ሊሆን ኣይችልም። በኣፉ ትንፋሽ እስኪያጥረው ድረስ ስለ ልማት ይለፍፋል። በተግባር ግን ኣዲስ መሬት ወይም ኣካባቢ ማልማት ይቅርና ተፈጥሮ በራሷ ፈቃድ ያለማችውን ኣካባቢ እንኳዋን መንጥሮ ኣልያም ኣቃጥሎ በማራቆት ነው የሚታወቀው። በጥቅጥቅነቱ የሚታወቀውን የጪሊሞ ደን መንጥሮ እንጨቱን ወደ ሌላ ክልል መጫኑ ለዚህ ኣንድ ትልቅ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው። የደኑን ሃብት መንጥሮ ለመጫን ኣላመች ባለው ኣካባቢዎች ደግሞ እሳት ለኩሶበት ወደ ኣመድነት መቀየር ኣንዱ የወያኔ መለያ ጠላታዊ ተግባሩ ነው።

ይህን የመሰለ በተፈጥሮ ኣካባቢ ላይ ያነጣጠረ ጠላታዊ እርምጃ በመውሰድ የሚታወቀው የመለስ ዜናዊ ስርኣት የኣለማችን የሙቀት መጠን መጨመር (Global warming) ከሚያሳስባቸው ኣለም ኣቀፍ ወገኖች ጋር የኣዞ እንባ ሲያነባ ማየቱ በርግጥ ኣሳፋሪ ነው። በፕሮጀክቱ ስም ከሃብታሞቹ ሃገራት ለድሆቹ ሃገሮች የሚለቀቀውን በቢሊዮኖች ዶላር የሚገመት ገንዘብ ነጥቆ ወደ ግል ካዝናው ለመጨመር ያሰፈሰፈው መለስ ዜናዊ በተቃራኒው በኢትዮጵያ እየፈፀመ ያለውን ወንጀል ያልነቁበትን የዋህ የኣፍሪካ ሃገራት መሪዎችን ለማጃጃል ሲጥር ይታያል።

የመለስ ዜናዊን ስርኣት ከቀደሙት የሃገሪቷ ገዢዎች ለየት የሚያደርገውን ኣንድ ነጥብ እዚህ ግድም መጥቀስ ኣስፈላጊ ይሆናል። የወያኔ ስርኣት ስልጣን ከያዘበት ወቅት ኣንስቶ የትግራይን ክልል በማልማት ከበረሃማነት ኣላቅቆ ወደ ኣረንጉዋዴነት እየቀየረ ይገኛል። ይህም እሰዬው የሚባል እንጂ የሚወገዝ ተግባር ኣይደለም። ይሁን እንጂ ትግራይን ከበረሃማነት ለማላቀቅ የተቻለለትን ጥረት ሁሉ በሚያደርግበት ተመሳሳይ ወቅት ቀደም ሲል በልምላሜዋ የምትታወቀውን ኦሮምያ ወደበረሃማነት ለመቀየር ያላሰለሰ ጥረት ተያይዞኣል። በዘር ላይ የተመሰረተው ይህ የስርኣቱ ኣደገኛ ፖሊሲ ነው ቀደም ሲል ስልጣን ላይ ከነበሩት ገዢዎች ለየት የሚያደርገው።

የኦሮሞ ህዝብ በመሰረቱ የተፈጥሮ ኣካባቢን የማልማት ባህላዊ ልማድ ያለው ህዝብ ነው። ኦሮሞ *ሰፉ* የሚባል ባህል ኣለው። በዚህ ባህል መሰረት ገና በእድገት ላይ የሚገኝ የዛፍ ተክል ተቆርጦ እድገቱ እንዲቁዋረጥበት ኣይደረግም። ኣንድ ትልቅ ዛፍ ሊገለገልበት በሚቆርጥበት ወቅትም ሌላ ዛፉን የሚተካ ችግኝ መትከል ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የኦሮሞ ህዝብ ባህል ነው። ተራቁቶ ወደ በረሃማነት የተቀየረን ኣካባቢ እንዴት መልሶ ማልማት እንደሚቻልም ኦሮሞ ልምድ ማካፈል የሚችል እንጂ ከሌላ የሚማር ህዝብ ኣይደለም። የተፈጥሮ ኣካባቢን እንዴት ማልማት እንደሚቻልና ከደን የሚገኘውን ጥቅም በተመለከተ የኦሮሞ ህዝብ ከዛሬው ሳይንስ የቀደመ ባህላዊ ኤክስፐርትነትን የተላበሰ ህዝብ ነው ቢባል በጭራሽ ማጋነን ኣይሆንም። ለዚህ ደግሞ ትልቅ ኣብነት ሊሆን የሚችለው ዛሬ በኣፍሪቃ ቀንድ ከሚገኘው የደን ሃብት ሽፋን ኣብዛኛው የሚገኘው በኦሮምያ መሆኑ ነው። ይህ በኣጋጣሚ የተፈጠረ ክስተት ሳይሆን የኦሮሞ ህዝብ ለደን ኣያያዝ ያለው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህላዊ ኣመለካከቱ ከሌሎች የቀጣናው ነዋሪ ህዝቦች በተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ነው። ምናልባትም ወያኔዎቹ በየጊዜው በኦሮምያ ደኖች ላይ እሳት እየለኮሱ

የሚያወድሙት በዚህ ቀንተው ሳይሆን አይቀርም በማለት አንዳንድ ወገኖች የሚያቀርቡት አስተያየት ከሃቅ የራቀ አይመስልም።

ባሁኑ ሰአት እጅት አንገብጋቢው ነገር በደቡብ ምስራቅ ኦሮምያ በወያኔዎች እሳት እየነደዱ ያሉት ደኖች ጉዳይ ነው። የህወሃት መንግስት ዛሬም በሃገሪቷ በተለይም በኦሮምያ ሰብአዊ ውድመት መፈፀሙ ሳያንሰው ምንም ባላጠፋው የኦሮምያ ደን ላይም እሳት ለኩሶ ወደ አመድነት እየቀየረው ነው። ባጭሩ ኦሮምያ በወያኔዎች የማን አለብኝነት እሳት እየነደደች ነው። ስለሆነም ባሁኑ ጊዜ እሳት ተለኩሶባቸው እየነደዱ ላሉት ደኖች ቅርበት ያላቸው ነዋሪዎች በፍጥነት እየተረባረቡ እሳቱን የማጥፋት የዜግነት ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማስታወስ እንሻለን። በተለይም ወጣቱ ትውልድ ልክ እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ አሁንም የተፈጥሮ አካባቢውን ወደ ምድረ በዳነት በመቀየር ላይ ያለውን አደገኛ የወያኔዎች እሳት ለማጥፋት ጊዜ ሳያባክን መረባረብ ይኖርበታል። መላው ሃገሪቷን በተለይም ኦሮምያን በጥፋት እሳቱ ወደ ምድረ በዳነት ለመቀየር አቅሙን አሟጥጦ በመንቀሳቀስ ላይ ያለውን የወያኔ ስርአት ከስር መሰረቱ ነቅሎ ለመጣል የሚደረገው ትግልም ከዚሁ ጎን ለጎን መፋፋም አለበት እንላለን።

*ድል ለኦሮሞ ህዝብ!*

*የኦነግ ኢንፎ ዴስክ*